CITY OF CAMBRIDGE | TPT Traffic, Parking, and Transportation

# የBroadway ደኅንነትን ማሻሻያ ፕሮጀክት

የተለዩ የብስክሌት መንገዶች እና ሌሎች የደኅንነት ማሻሻያ ሥራዎች
ከQuincy St. እስከ Portland St.

## የመንገድ አቀማመጥ ለውጦች

የCambridge ከተማ አስተዳደር የተለዩ የብስክሌት መንገዶችን የመጨመር እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ የደኅንነት ማሻሻያዎችን የማድረግ ሥራ ይሠራል። የሚከተሉትን ሥራዎች የምንሠራ ይሆናል፦

**የተለዩ የብስክሌት መንገዶችን የመገንባት ሥራ፦**
ይህ ሥራ ማለት ከተሽከርካሪዎች በነጭ ተጣጣፊ ምሰሶዎች ወይም በሌሎች ቁሶች የተለዩ የብስክሌት መንገዶችን በመንገዱ ጠርዝ በኩል የመገንባት ሥራ ማለት ነው።

**የትራፊክ ፍሰት የማረጋጋት ሥራን መጨመር፦**
በአውቶብስ ለሚጓዙ እና በእግራቸው ለሚሄዱ ሰዎች የታሰቡ ለውጦች፦ የአውቶብስ መቆሚያ ፎርማታ ለውጦች ሊኖሩ የሚችሉ ሲሆን፣ እግረኞችን ታሳቢ አድርገው የሚሠሩትም የደኅንነት ማሻሻያዎች የእግረኛ መንገዶችን የተሻሉ ያደርጓቸዋል።

**የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን መቀነስ፦**
ይህ ፕሮጀክት መንገድ ላይ መኪና ማቆም የሚቻሉባቸውን ቦታዎች ይቀንሳል። ንድፍ የማውጣት ሥራው ገና ባይገባደድም፣አሁን ካሉት መኪና ማቆሚያ ቦታዎች መካከል ግን 40% የሚሆኑትን የማቆየት፣ መኪና ማቆም የሚቻለውም በአንዱ በኩል ብቻ እንዲሆን የማድረግ ዕቅድ ይዘናል

በፕሮጀክቱ ድህረ ገጽ ላይ በፕሮጀክቱ ዙሪያ ወቅታዊ መረጃዎችን ማግኘት ይችላሉ

ወቅታዊ መረጃዎችን በኢሜል ለመቀበል ይመዝገቡ

## በቅርብ ቀን የሚካሄዱ የማኅበረሰብ ዝግጅቶች

ይምጡ ስለ ፕሮጀክቱም ይወቁ፣ አስተያየትዎንም ይስጡ። የመጀመሪያዎቹን ዕቅዶች የምናጋራ፣ በፕሮጀክቱ መርሃ-ግብር ዙሪያ እና ፕሮጀክቱ ስለሚያስገኛቸው ጥቅሞች እንዲሁም ስለሚያመጣቸው ለውጦች የምንወያይ ይሆናል።

**ማክሰኞ፣ ጃኑዋሪ 28 ቀን 2025 ዓ.ም**
6 ፒ.ኤም - 8 ፒ.ኤም
የማኅበረሰብ ቨርቹዋል (ምናባዊ) ስብሰባ
Zoom (ዙም)

**ማክሰኞ፣ ፌብሩዋሪ 4 ቀን 2025 ዓ.ም**
4 ፒ.ኤም - 6 ፒ.ኤም
ለሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት ክፍት የሆነ በአካል የሚደረግ ስብሰባ #1
Fletcher-Maynard አካዳሚ
225 Windsor St.

**ሐሙስ፣ ፌብሩዋሪ 6 ቀን 2025 ዓ.ም**
6 ፒ.ኤም - 8 ፒ.ኤም
ለሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት ክፍት የሆነ በአካል የሚደረግ ስብሰባ #2
City Hall ግቢ ውስጥ የሚገኘው ሁለተኛው ሕንፃ፣ ሁለተኛ ፎቅ
344 Broadway

**CITY OF CAMBRIDGE** | **TPT** Traffic, Parking, and Transportation

# የBroadway ደኅንነትን ማሻሻያ ፕሮጀክት

የCambridge ከተማ አስተዳደር Broadway ላይ የተለዩ የብስክሌት መንገዶችን ለመጨመር እና ተዛማጅ የደኅንነት ማሻሻያ ሥራዎችን ለመሥራት እያቀደ ይገኛል። እስካሁን ስለ ፕሮጀክቱ ምን እናውቃለን?

# ምን ዓይነት ለውጦች ይደረጋሉ?

የሁሉም ተጠቃሚዎች ደኅንነት ይሻሻላል፣ የተለዩ የብስክሌት መንገዶች ይሠራሉ፣ በአገናኝ መንገዱ (ኮሪደሩ) ላይ መኪና ማቆም የሚቻልባቸው ቦታዎችም ይቀነሳሉ

## የታቀደው የመንገድ አቀማመጥ

ባለ አንድ ጎን የመንገድ ላይ የመኪና ማቆሚያ እና እያንዳንዱ ጎን ላይ በአንድ በኩል ብቻ መሄድ የሚቻልባቸው የብስክሌት መንገዶች የያዘ።

## ፕሮጀክቱ የሚሸፍነው ቦታ ካርታ

ፕሮጀክቱ የሚሸፍነው ቦታ Broadway ላይ ከQuincy St እስከ Portland St ድረስ ያለውን ቦታ ነው።







## የመንገድ ላይ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን የመቀነስ ሥራ

ይህ ፕሮጀክት መንገድ ላይ መኪና ማቆም የሚቻልባቸውን ቦታዎች ይቀንሳል። ንድፍ የማውጣት ሥራው ገና ባይገባደድም፣ አሁን ካሉት መኪና ማቆሚያ ቦታዎች መካከል ግን 40% የሚሆኑትን የማቆየት ዕቅድ ይዘናል።

## የተለዩ የብስክሌት መንገዶች

የብስክሌት መንገዶች ከመንገዱ ጠርዝ አጠገብ እንዲሆኑ፣ በእንቅስቃሴ ላይ ካሉ ተሽከርካሪዎችም ነጭ ቀለም ባላቸው ተጣጣፊ ምሰሶዎች እንዲለዩ እናደርጋለን።


awolfe@cambridgema.gov
www.cambridgema.gov/BroadwaySafety